# ኢት-ኢኮኖሚ ET- ECONOMY

ዐ/ት ፂዮን ዘ/ማርያም

ክፍል አንድ

ከትግራይ ምሁራን ምላሽ ሊሰጡበት የሚገባ የኢኮኖሚ ብዝበዛ በኢትዩጵያ ያስከተለው ህዝባዊ እንቢተኝነት

ዓሣ ጎርጎሪ ዘንዶ አወጣ
የሰው ፈላጊ የራሱን አጣ!!!

## ከህዝባዊ እንቢተኝነት ወደ የኢኮኖሚ ማእቀብ

በኢትዩጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት፣ሁሉም ክልሎች የየራሳቸውን የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ፣ እቅድ መንደፍ ቢችሉም የሃብታቸው ተጠቃሚ የመሆን ነፃነት የላቸውም፡፡ የክልላዊ ኢኮኖሚ እቅድ ነድፈው በአጭርና ረጅም ግዜ ሊፈፅሙ የሚገባቸውን መፍትሄዎችና ግቦች ለህዝብ በማሳወቅ በክልላቸው ኢኮኖሚ የመጀመሪያ ተጠቃሚ ሆነው በሃገራቸው የመኖር ነፃነትና የኢኮኖሚ ዋስትና በፌዴራላዊ መንግስት አልተረጋገጠላቸውም፡፡ በኢትዩጵያ ቋንቋ ተኮር ፌዴራላዊ ስርዓት ክልሎች ምን ዓይነት የተፈጥሮ ኃብት እንዳላቸው፣ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት፣በግብርናው ዘርፍ ምን ያህል ሚሊዩን ኩንታል ሰብል ያመርታሉ በማኑፋክቸሪንግና በአገልግሎት ዘርፍ ምን ያህል ምርት ያመርታሉ? ለውጭ ንግድ የሚያቀርቡት ብና፣ሰሊጥ፣ቦለቄ፣የቁም እንሰሳት፣ወርቅ ወዘተ ምርቶች የሚያስገኙት የውጭ ንግድ ድርሻና የውጭ ምንዛሪ ምን ያህል ነው የክልሉ ህዝብ ላበረከተው የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ምን አገኛ

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በክልሉ ምንያህል ኢንቨስትመንት/መዋዕለ-ነዋይ ፈሶል? ለምን ያህል ሰዎች የስራ ዕድል ተፈጥሮል? በአገልግሎት ዘርፍ ምን ያህል ኢንቨስተሮች ተሳትፈዋል? የክልሉ መንግስት የባህር ሞዶ ኢንቨስተሮችን ምን ያህል ስቧል በክልሉ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት ምንያህል ነው የክልሉ መንግስት በህዝብ ማህበራዊ ልማት ተደራሽነት ማለትም በመሠረተ-ልማት፣ መንገድ፣ባቡር፣የአይሮፕላን ማረፍያ የኤሌትሪክ፣ የቴሌኮምኒኬሽን፣የትምህርት፣ጤና አገልግሎት ሽፋን ወዘተ ከሌሎች ክልሎች ጋር እንዴት ይነፃፀራል? በክልሎች መኃል ያለ የኢኮኖሚ እድገት ልዩነት እየሰፋ ነው እየጠበበ የሄደው? የክልሎች የህዝብ የነፍስ ወከፍ ድርሻ ልዩነት እንዴት ይገለፃል? በተፈጠረው የኢኮኖሚ ልማትና እድገት ምን ያህል ሰዎች የስራ እድል አገኙ? በየክልሎቹ የሚገኙ የግብርና፣የማኑ-ፋክቸሪንግ፣ የአገልግሎት፣ የባንክ አገልግሎት የብድር ፍላጎትና አቅርቦት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የክልሉ ህዝብ ላበረከተው የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ምን አገኛ የሚሉትን የህዝብ ጥያቄዎች የትግራይ ምሁራን ያለ አንዳች አድሎ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በኦሮሞ፣በአማራ በሌሎች ክልሎችም የህዝብ አንገዛም እንቢተኝነት የተነሳው ህወኃት/ኢህአዴግ መንግስት ስርዓት በሙስና በመዘፈቁና የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች መታፈን፣ የፕሬስ ነፃነት መታገድ፣ ፍትህና ርትህ፣ የህግ የበላይነት መጥፋት፣ የእኩልነትና የነጻነት መብቶች መጣስ፣ የህገ-መንግስቱ አለመከበር ናቸው፡፡

የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት፣የኢትዩጵያ ብሄራዊ ኢኮኖሚ እድገት እቅድ ትኩረት ባለማግኘቱ በክልል መንግስቶች መኃል የሃብት ክፍፍሉ ከአመት አመት እየጨመረ መጥቶል፡፡ የአንዱ ክልል ኃብት በጉልበተኛ ክልል ሃብቱ ሲዘረፍ 25 አመታት ተቆጠረ፡፡ በሃገሪቱ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ፕላን፣ ትኩረት ማግኘት አለመቻሉና የክልላዊ ዘውግ ተኮር ፍቅር ከብሄራዊ የኢትዩጵያዊ ሃገር ፍቅር በላይ መሆን የተነሳ በኢትዩጰጵያ ያልተመጣጠነ የኃብት ክፍፍልና ያልተስተካከለ የክልል መንግስታት ኢኮኖሚያዊ እድገት ብዙዎቹን ክልሎች ኃላቀር እንዲሆኑ አድርጎታል፡፡

የህወኃት ክልላዊ ዘውግ ተኮር ፍቅር የተነሳ የተለያዩ ክልሎችን የግብርና ምርቶች (ቡና፣ሠሊጥ፣የቅባት እህሎች፣ጫት፣ቅመማ ቅመም፣ የቁም እንሰሳት ወዘተ) ወደ ጎረቤት ሃገሮች በመላክ የውጭ ምንዛሪ ያግበሰብሳሉ ብሎም ገንዘቡን ወደ ባህር ማዶ ሀገራት ያሸሽሉ። የህወሃት /ኢህአዴግ የፌዴራልና ክልላዊ መንግስታት የፖለቲካ ካድሬዎችና የጦር አበጋዞች ሓብት ማግበስበስ ሲያፋጥን የክልሎችን የኢኮኖሚ እድገት ማሽቆልቆል የኃብት ክፍፍሉን ሚዛን ማዛባት፣ የአንድ ብሄር ጥቂት ልጅ እግር ባለፀጎች መፈልፈልና ብዙሃኑ ዜጋ ከድኅነት ወለል በታች እንዲኖር ምክንያት ሆኖል። ህዝብና የብሄራዊ ኢኮኖሚችንን እድገት ያቀጨጨ መሆኑን የሚጠራጠር ካለ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ያልተገነዘበ ምሁር ነው።በሃገሪቱ የሠፈነው የፌዴራልና የክልል መንግስታት የሞኖፖሊ ኢንፓየር የግሉ ዘርፍ ባለኃብት ስራን በመንጠቅ ኢኮኖሚውን በእዝ ኢኮኖሚ ጠርንፎ የያዘና የመሬት ኃብትን በመንግስት ስም የህወሃት /ኢህአዴግ ሹማምንቶች ንብረት በማድረግ ሰፊውን የኢትዩጵያ ህዝብ ጭሰኛ ያደረገ የክልሎች የጦር አበጋዞች ስርአተ አገዛዝ በህዝባዊ አመፅ ለመውደቅ እየተንገዳገደ ይገኛል።

ገነት ለመግባት ጋሃነመ-እሰት ማመልከቻ አይገባም!!!

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ

የኢትዬጵያ ኢኮኖሚ በ2006እንደ ኢትዬጵያ አቆጣጠር መሰረቱ የግብርናው ዘርፍ ኢኮኖሚ ሲሆን ከአጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ)40.2 በመቶ በማምረት፣ ከሃገሪቱ የውጭ ንግድ 80 በመቶ አስተዋፅኦ በማድረግ እንዲሁም የሰው ኃይል ልማት 80 በመቶ ሠራተኞች የሥራ እድል የፈጠረ ዘርፍ ነው። በሃገሪቱ የግብርናው ዘርፍ ኢኮኖሚ ሥራ የሚከናወነው በአነስተኛ የእርሻ መሬት፣ ዝቅተኛ ካፒታል፣ በኃላ ቀር የእርሻ መሣሪያዎች(በሬዎች ጠምዶ በማረስ )፣በዝቅተኛ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር አቅርቦት ፣በሃገሪቱ ገበሬዎች ጉልበትና ኃብት ላይ የተመሠረተ ነው። ገበሬዎች ገንዘብ የሚያስገኙ ምርቶችን ለምሳሌ ቡና፣ምስር፣የቅባት እህሎች (ሰሊጥ፣ ተልባ፣ቦለቄ፣ ኑግ ) ፣ ጥራጥሬ፣ጫት ወዘተ ያመርታሉ። የቡና ምርት የሃገሪቱ የውጭ ንግድ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ነው። ሃገሪቱ በበቆሎ ምርት ከአፍሪካ የሁለተኛ የአምራችነት ደረጃ ላይ ትገኛለች። በ2006እኢአ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ 14.3 በመቶና የአገልግሎት ዘርፍ 46.2 በመቶ ከአጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት (ጂዲፒ)ድርሻ እንዳላቸው ተገልጾል።

## ከህዝባዊ እንቢተኝነት ወደ የኢኮኖሚ ማእቀብ!!!

### የሰላም በር ሲዘጋ የአመጽ በር ይከፈታል!!!

የህወሓት/ኢህአዴግ የጦር አበጋዞች መንግስት ከህዝብ የተዘረፉ ኃብቶች በአዋጅ፣ በህግና ሥነ-ስርዓት የህዝብ ኃብት እንዲሆኑ በሃገሪቱ የኢኮኖሚ መርማሪ ኮሚሲዩን ማቆቆም አስፈላጊ ነው። በዚህም መሠረት በጥናት በሙስና የተዘረፍ ሓብቶችን የህዝብ ሃብት አርጎ መውረስ አርቆ አስተዋይነት ነው። እስከዚያው ህዝባዊ ትግሉ ፍሬ እዲሰጥ ከተፈለገ የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት የኢኮኖሚ የገቢ ምንጮችን ህዝቡ በኢኮኖሚ ማእቀብ ገቢያቸውን ሲያደርቅና አንባገነኑ መንግስት ከስልጣን ሲያስወግድ ብቻ ነው።

{1} የውጭ ንግድ ገቢ ማንጠፍ፣ ሃገሪቱ በውጭ ንግድ የምታገኘው አመታዊ ገቢ ከ2.5 እስከ 3 ቢሊዩን ዶላር ይገመታል፣ይህ ገቢ የሚነጥፈው የሃገሪቱ ገበሬዎች የሚያመርቱትን ምርቶች በተለይ ቡና፣ ሰሊጥ፣ቦለቄ፣ጫት፣የቅባት እህሎች፣ የአበባ ምርት፣ የቁም እንስሳቶች ወዘተ ለውጭ ንግድ ግብይይት ባለማቅረብ በውጭ ንግድ የሚገኘውን ገቢና የውጭ ምንዛሪ ማሳጣት ይችላል።

የውጭ ንግድ ገቢ በኢትዩጵያ ኢዩሮ ሚሊዩን

| | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዩጵያ | 237 | 8 | 1327 | 1612 | 1674 | 2520 | 2614 | 3142 | 3047 |

ምንጭ፣ የአውሮፓ ህብረትና የአፍሪካ ህብረት ስታስቲካል ቡክስ 2014 ህትመት ገፅ 94

የምግብ ዋስትና በኢትዩጵያ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ አልተቻለም በ2008 ዓ/ም 270 ሚሊዩን ኩንታል ሰብል በማምረት በመቻሉና በህዝቡ አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ሲሰላ 3 ኩንታል መሆኑ በጣም ኢምንትና አነስተኛ መሆኑ አያከራክርም። ለዚህ ነው የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት በ25

አመታት አገዛዝ ዘመኑ፣በሃገሪቱ የርሃብ ዘርን እየዘራ ከዓለም ህዝብ የእህል እርዳታ በመለመን ራሳቸውን በሃብት በማበልጸግ በከተሞች ፎቆች ሲገነቡና ሃብት ሲያግበሰብሱ ይስተዋላሉ፡፡ህዝቡን መመገብ ያልቻለ መንግሰት ህዝቡን መግዛት አይችልም!!!

የቡና ምርት፣ ጥቁሩ ወርቅ "black gold" በሃገሪቱ የውጭ ንግድ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ነው፡፡ከግብርና ዘርፍ የቡና ምርት 62 በመቶ ሚሆነውን የውጭ ንግድ የሚሸፍን ሲሆን ከፍተኛውን የውጪ ምንዛሪ የሚያስገኝ ዘርፍ ነው፡፡ሃረሪቱ በውጭ ንግድ ከቡና ምርት ብቻ ከ600 እስከ 900 ሚሊዩን ዶላር ታገኛለች፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ከኢትዩጵያ የውጭ ንግድ ሽፋን ድርሻ በቡና የ60 በመቶ፣ የሃገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ኃብት ገቢ ያስገኛል፡፡ የኦሮሞ ህዝባዊ እንቢተንነት ቡናው ከክልሉ እንዳይወጣ ካደረገ ገቢው ደረቀ ማለት ነው፡፡

የአበባ ምርት በሃገሪቱ 95 በመቶ የአበባ ምርት የሚመረተው በኦሮሞ ምድር ነው፡፡ ለምሳሌ በ2014 እኤአ ኢትጵያ በውጭ ንግድ የላከችው የአበባ ምርት 45,000 ሜትሪክ ቶን ሲሆን 187 ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር ለሃገሪቱ የኦሮሞ ህዝብ አስገኝቶል፡፡ ህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት ታዲያ የኦሮሞን ታታሪ ህዝብ ኃብቱን እየዘረፉ፣ መሬቱን እየነጠቁ፣ ከብቱን እየነዱ፣ ሰውን እየገደለ መኖር ይፈልጋል፡፡

የእንሰሳ ኃብት

ኢትዬጵያ በእንሰሳ ኃብት ልማት ከአፍሪካ አንደኛ እንዲሁም ከአለም አስረኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ኢትዩጵያ 52.1 ሚሊዩን የቀንድ ከብቶች፣ 24.2 ሚሊዩን በጎች፣ 22.6 ሚሊዩን ፍየሎች፣ 987 ሽህ ግመሎች፣44.9 ሚሊን ዶሮች፣5 ሚሊዩን የንብ ቀፎ ኃብት እንዳላት ጥናቶች ይገልፃሉ፡፡ የእንሰሳ ኃብትና ቆዳና ልዩ ል ቆዳ ነክ ምርቶች፣ቆዳ፣ሥጋ ምርት፣የቁም እንሰሳ በውጭ ንግድ 11 በመቶ ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡በ2014 እኤአ ኢትዩጵያ ከእንስሳ ኃብቶ፣ በውጭ ንግድ 250 ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር ገቢ አግንታለች፡፡

| ኢትዩጵያ | | |
|---|---|---|
| ተ/ቁ | ዓይነት | ብዛት |
| 1 | የቀንድ ከብት cattle | 52,1 million |
| 2 | በግ sheep | 24,2 million |
| 3 | ፍየል goats | 22,6 million |
| 4 | ግመል camels | 987,000 |
| 5 | ዶሮ poultry | 44,9 million |
| 6 | ንብ ቀፎ beehives | 5 million |

Ethiopia has the largest livestock population in Africa and among the top eight countries in the world.
The country has 52,1 million cattle, 24,2 million sheep, 22,6 million goats, 987.000 camels, 44,9 million poultry and nearly 5 million beehives. Livestock and related products account for over 11% of the national export earnings. Leather, meat and live animals are the principal exportable livestock products.
Livestock and related products account for over 11% of the national export earnings. Leather, meat and live animals are the principal exportable livestock products. Live animals and meat production is another investment area within the livestock sector. It offers opportunity to serve a vast export market to the Middle East as well as the domestic market. Ethiopia earned US $250 million from export of meat and live animals in 2014. Lowland pastoralists produce the largest share of meat and live animals for export: they account for 90% of all such production in Ethiopia.
የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት በህገወጥ አጎራባች ሃገርት ማለትም ሱማሌያ፣ ጅቡቲ፣ኬንያ፣ ሱዳንና፣ ደቡብ ሱዳን ሃገራት የቀንድ ከብቶች ማለትም ግመሎች፣ በጎችና፣ፍየሎች ወዘተ በጠረፍ ንግድ በህገወጥ መንገድ በማድረግ ከ250እስከ 300 ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር በአመት (መንግስት ከሚገልፀው መቶ እጥፍ በላይ ሕገወጥ የጠረፍ ንግድ)ይካሄዳል፡፡ በዚህም የተነሳ ሃገሪቱ የገቢ ታክስና የውጭ ምንዛሪ ገቢዎን ታጣለች፡፡

Cross-border trade by pastoralists is often informal and beyond state control and regulation. In East Africa, over 95% of cross-border trade is through unofficial channels. The unofficial trade of live cattle, camels, sheep, and goats from Ethiopia sold to Somalia, Djibouti, and Kenya generates an estimated total value of between 250 and 300 million USD annually (100 times more than the official figure).[132]
Furthermore, the government of Ethiopia is purportedly unhappy with lost tax revenue and foreign exchange revenues.[132] Recent initiatives have sought to document and regulate this trade.[132]

{2} የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መንጠፍ የባህር ማዶ ኢንቨስተሮች ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ህዝባዊ ትግል ምክንያት ሰላም ከሌለ ኢንቨስተሮቹ ስራቸውን ማከናወን ስለማይችሉ አገሪቱን ጥለው ይወጣሉ፣

የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በኢትዩጵያ

| | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዩጵያ | 2.1 | 0.9 | 2.0 | 2.6 | 1.7 | 1.3 | 0.9 |

ምንጭ፣ የአውሮፓ ህብረትና የአፍሪካ ህብረት ስታስቲካል ቡክስ 2014 ህትመት ገፅ 92

{3} የቱሪስቶች መታቀብ ሃገር ውስጥ በሆቴልና ቱሪዝም የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከ 3 ቢሊዩን ዶላር በላይ ገቢ በህዝባዊው ትግል የተነሳ ቱሪስቶች ሰላም ከሌለ ስለማይመጡ ይነጥፋል፡፡ የብዙ አገሮች መንግስታት የአሜሪካን፣ የአውሮፓ መንግስታት በተደጋጋሚ ዜጎቻቸውን ወደ ኢትዩጵያ እንዳይሄዱ ከአሁኑ በመምከር ላይ ይገኛሉ፡፡

{4} የወርቅ ማዕድን ኃብት ከሃገር እንዳይወጣ ማድረግ፣ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ ወርቁ ከሃገር እንዳይወጣ በማድረግ ከ500 እስከ 750 ሚሊዩን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ገቢ ወያኔን ማሳጣት ይቻላል፡፡
የሜድሮክ የለገደንቢና የመተከል ዞን ጂላ የወርቅ ማዕድናት፣የወያኔ የኢፈርት ኢዛና የወርቅ ማዕድን የሥራ እንቅስቃሴን መግታትና ማደናቀፍ ያስፈልጋል፡፡ በውጭ ንግድ ወርቁ ካልተላከ የሃገሪቱ ኢኮኖሚው ይወድቃል፡፡

ወደ ውጭ የተላኩ/የኤክስፖርት የወርቅ ማዕድን ምርት ዋጋ ('000 በሚሊዩን ብር)

**Table 1: Value of Exports by Major Export Commodities**

Value of Export ('000 Birr), 2005 – 2009

| Export Commodities/ የኤክስፖርት ምርቶች | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 5-years Average | Average % Share |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Gold /**ወርቅ** | 385,038 | 447,822 | 458,033 | 768,717 | 1,074,994 | 626,921 | 5 |
| **Annual** Export **Total** | **7,698,132** | **8,785,619** | **10,705,887** | **14,946,011** | **17,733,396** | **11,973,809** | 100 |

- 

ከ2005 እስከ 2009 እኤአ ባህር ማዶ የተላከ የወርቅ ማዕድን ምርት በ2005 (385,038,000 ሚሊዩን ብር)፣2006 (447,822,000 ሚሊዩን ብር)፣2007 (458,033,000 ሚሊዩን ብር)፣2008 (768,717,000 ሚሊዩን ብር)፣2009 (1,074,994,000 ቢሊዩን ብር)፣ የአምስቱ አመት አማካይ (626,921,000 ሚሊዩን ብር) ነበር፡፡ ከኢትዩጵያ ወደ ውጭ ከተላከው አጠቃላይ ኤክስፖርት የወርቅ ማዕድን ምርት ድርሻ አምስት (5%-7.5%) በመቶ ድርሻ እንደ ነበረው መረጃው ያሳያል፡፡

{5} የንግዱ ማህበረሰብ ከወያኔ የከተማ ቦታ የመሬት ሊዝ ጨረታ ባለመሳተፍ በህዝባዊ እንቢተኛነት የተሰው ሰማዕታቶችን ደም ክብር መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የንግዱ ህብረተሰብ በአዲስአበባ ከተማና በክልሎች ከተማዎች በወያኔ ቤታቸው የፈረሰባቸውን ዜጎች መሬት ለመግዛት በሊዝ ጨረታ ሲጫረቱ የወገናቸው ስቃይና ሐዘን ቆርቁሮቸው በዚህ መልክ ዜጎችን አፈናቅሎ፣ቤተሰባቸውን በትኖ፣ ዜጎችን የመንገድ ላይ ተዳዳሪ ላደረገ የወያኔ መንግስት በአመት በብዙ ቢሊዩን ብር የሚቆጠር የመሬት ሽያጭ ገቢ በማስገኘታችሁ ወያኔን መንግስት በተዘዋዋሪ እየረዳችሁ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባችሆል፡፡ ወያኔ ሽበጥ ጫማ ተጫምቶ፣ቁምጣ ሱሪ ታጥቆ፣ መሳሪያ አንግቦ ስልጣን የያዘ የማፍያ ቡድን ዛሬ በአዲስአበባ ከተማና ሌሎች ከተሞች ፎቆች ገንብቶ፣ ቪላ ቤቶች እያከራየ፣ የመንግስት መኪና እየነዱ፣ በሙስና የህዝብ የከተማ መሬት እየሸጡ የከበሩ ወሮበላዎች ቡድን፣ ህዝቡን ህገወጥ ቤት ሠራችሁ እያለ የህብረተሰቡን ቤት የማፍረስና የመሸጥ የማራል ብቃትና በህግ ስልጣን ያለው መንግስት አይደለም፡፡ ይህን አንባገነን ፋሽስታዊ ስርዓት እየተዋጋ ህይወቱን ከሚሰዋው ወገናችሁን ጎን ወግናችሁ ማገዝ የዜግነት ግዳጅ አለባችሁ፡፡ የንግዱ ህብረተሰብ ህዝባዊውን ትግሉን በዚህ መልክ መቀላቀል ይጠበቅባችሆል፡፡

{6} ምእመናን ከእምነት ቦታዎችን አለመሄድ፤ የኢትዩጵያ የሃይማኖት አባቶች ማለትም፣ የክርስትና፣የእስልምና፣ የኮቶሊክ የሃይማኖት አባቶቸች በየሠላማዊ ሠልፉ፣ በህዝባዊ ትግል መስዋት ለሆኑ ወገኖች መንግስትን በመቃወም ተቃውሞችሁን ሳታሰሙ በአድርባይነት አቆማችሁ ከምእመናኑ ጎን አልቆማችሁም፡፡ የሃይማኖት ቤተ-እምነቶች ከህዝቡ የሚያገኙት በአመት በብዙ ቢሊዩን ብር ገቢ ከእምነቱ ተከታዬች መሆኑን አውቃችሁ ተቃውሞችሁን ማሰማትና ከህዝብ ጋር መወገን ይጠበቅባችኃል፡፡ ይህ በተግባር እስካልተገለፀ ድረስ የእምነቱ ተከታዩች ከቤተ-ክርስቲያኖች፣ ከመስጊዶችና ከሌሎች የእምነት ፀሎት ቤቶች

ባለመሄድና ምእመናኑ ስለት፣መባ፣አስራት፣ መዳየ-ምዕዋት፣ የመሳሰሉትን የገንዘብ እርዳት ባለማድረግ በህብረት ቃል በመግባት፣ ለወደቁት ሰማዕታት ከቤታችሁ ሆናችሁ ፀሎት ማድረግ ይጠበቅባችሆል።

{7} ዘመን መለወጫ፣የ2009 ዓ/ም የአዲስአመት ዘመን መለወጫ እንቁጣጣሽ ባሃል ዝግጅት ለማድረግ ሽር ጉድ በሚባልበት የዓመት ባህል ላይ ባለመገኝት፣ በህዝባዊው አብዬት ትግል የወደቁ ሰማዕታቶችን ማስታወስ ተገቢ ስለሆነ በዚህ የዳንኪራ ስነ-ሥርአት ላይ ባለመገኝት የዜግነት ግዳጃችንን መወጣት ይጠበቅብናል።

{8} የብሄራዊ ሎተሪ ትኬት አለመግዛት፣የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት በህዝባዊ እንቢተኝነት ትግል ለመንግስት ግብር ባለመክፈል፣ የብሄራዊ ሎተሪ ትኬት በመሸጥ ወያኔ የሚያገኘውን በትንሹ 75ሚሊዩን ብር ገቢ ህዝቡ ትኬቱን ባለመቁረጥ ገቢ በማሳጣት፣ትግሉን መግፋትና መንግስትን መጣል ይችላል።

{9} ከፓርቲ የንግድ ድርጅቶች እቃ አለመሸመት፣የህወሃት ኢፈርት፣የሜቴክ፣ ፣የብአዴን ጥረት፣የኦፒዲኦ ቱምሳና የደቡብ ወንዶ የፓርቲ የንግድ ድርጅቶች፣እንዲሁም ከሜድሮክ፣የንግድ ግዥ እቀባ በማድረግ ህዝባዊ ትግሉን ማጠናከር።

{10} የለሊቱ ህዝባዊ እንቢተኝነትን፣አድማን ከቤት ውስጥ ሆኖ ማስቀጠል፣ ከለሊቱ አራት ሰዓት ላይ የፊሽካ፣የፉጨት፣ የማንኮኮት፣የኡኡታ፣ የጡሩንባ የጩኸት አድማ በማድረግ የተቀጣጠለውን የኦሮሞና የአማራ ህዝባዊ እንቢተኝነት መቀላቀል የሁሉም ዜጎች የውዴታ ግዴታ ነው። ስለዚህ በህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት፣ በአጋዚ ጦር ተጠርንፈን ያለን ዜጎች ሁሉ ወያኔን ለዓለም ህብረተሰብና ለዓለም አቀፍ ድርጁቶች፣ለአፍሪካ ህብረት፣ ለአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በአፍሪካ፣ ለተለያዩ ኢንባሲዎች ወዘተ ወያኔን ለማጋለጥ በአዲስ አበባ፣ አዳማ፣ ብሸፍቱ፣ በድሬዳዋ፣በሃረር፣በመቀሌ፣በደሴ፣በአዋሳ፣አርባ ምንጭ፣ደብረብርሃን፣ጎንደር፣ ብህር ዳር፣ለቀምት፣ ወዘተ ከተሞች ውስጥ የለሊት ህዝባዊ አድማውን በማድረግ ህዝባዊ ትግሉ ትግላችን መሆኑን ማሳየት የዜግነት ግዳጃችን ነው። ህዝባዊ እንቢተኝነቱ በጳጉሜ አንድ እስከ አምስት 2008ዓ/ም፣ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ይጀመራል።

{11} ኢትዮጵያዊያን ድረ-ገፆች የጥላቻ ፖለቲካ፣ የዘር ፍጅት (ጀኖሳይድ) የሚሰብኩ ፁሁፎችን ባለማስተናገድ የዜግነት ምሁራዊና የጋዜጠኝነት ሙያዊ ግዴታችሁን መወጣት ይጠበቅባችኃል።

{12} የብዙኃን ማህበራቶችን በህዝባዊ አመፅ ማሳተፍ፣ የመምህራን ማህበር፣የሠራተኛ ማህበር፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ የታክሲ ማህበር፣የመንግስት ሠራተኞች፣ ወዘተ በህዝባዊ ትግሉ እንዲሳተፉና በሚስጢር እንዲደራጁ ማድረግ ያስፈልጋል።

{13} ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያዎች የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት፣የዛሬ 25 አመት ህገወጥ የጦር መሳሪያዎች ታጥቀው ደርግን በመጣል በትረ-ሥልጣኑን ያዙ። በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም ሆነና አዲስ ዘመን ጋዜጣ ነሐሴ 21 ቀን 2008 ኣ/ም (ህገ ወጥ የጦር መሳሪያዎችና ግጭት) በሚል ርእስ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በ2008 ዓ/ም አንድ ሚሊዩን 515 ሽህ ብር የሚገመት ህገወጥ የጦር መሣሪያ መያዙን ማመልከቱም አገሪቱ የችግሩ ተቆዳሽ ስለመሆኖ ይጠቁማል። በጉዳዩ ለይ የተደረጉ ጥናቶችም ስለ አሳሳቢነቱ ፍንጭ ይሰጣሉ።

እአአ በ2011 በአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ስር ለሚገኘው የሰላምና ደህንነት ጥናት ተቋም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሞያ በሐኔታ ገብረመድሕን (አሁን ረዳት ኮሚሽነር) የተሰራው ጥናት እንደሚያትተው፣ ወደ አፋር ክልል በተለያየ መንገድ የሚገባው ህገወጥ የጦር መሣሪያ በጎሳዎች መካከል ለሚካሄደው ግጭት የሚያበረክተው አስተዎፅኦ ከፍተኛ ነው። በክልሉ የተመዘገበውንም ሆነ ያልተመዘገበውን የመሣሪያ ብዛት የሚያሳይ ትክክለኛ አሃዛዊ መረጃ የለም።

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል አማካሪ የሆኑት ረዳት ኮሚሽነር ሐኔታ ገብረመድህን የተጠቀሱትን ጉዳዩች የሚያጠናክሩ አስተያየት አላቸው።‹‹ የደርግ ሰራዊት ሲበተን እሰከ 500 ሽ የሚደርስ ቀላልና መካከለኛ የጦር መሳሪያ ይዞ እንደነበር ይገመታል።›› በማለት ከእነዚህ ውስጥ 88 በመቶው ገቢ ሲሆን 12 በመቶው በተለያየ መንገድ በግለሰቦች እጅ በህገ ወት መንገድ እንደተያዘ የሚያመለክት መረጃ መኖሩን የጠቁማሉ።ይህም 60000 ሽህ የጦር መሣሪያ በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እጅ እንዲገባ እድል መፈጠሩን ያመላክታል።

ኮሚሽነር ሐነኔታ ህገወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ከአመት ወደ አመት እያደገ የመጣ መሆኑን በማንሳት፣‹‹በ2003 ዓ/ም 26000 ሽህ 485 ልዩልዩ ጠመንጃዎች፣ ሽጉጦች፣ጥይቶች፣ቦንቦችና የቡድን መሣሪያዎች በፎዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አማካኝነት ተይዘዋል። ይህ አሃዝ በ2007 ዓ/ም ወደ 33000 ሽህ 298 አድጎል።›› ይላሉ።

እንግዲህ በመላ ሃገሪቱ ‹‹ህገ ወጥ›› የጦር መሣሪያ ዝውውር በአማራ ክልል ክልሉ ከሱዳን ጋር ሰፊ ድንበር የሚዋሰን በመሆኑ፣በሱማሌ ክልል ከጅቡቲና ሱማሌ ግዛቶች ጋር ኩታ ገጠም ድንበር በመኖሩ፣ በጋምቤላ ክልል በኩል ክልሉ ከሱዳን ጋር መዋሰኑ፣በትግራይ ክልል በኩል ከኤርትራ ጋር ድንበር ስለሚጋራ፣ የደቡብ ህዝቦች ክልል በኩል ኬንያና ሱዳን ስፊ የድንበር የሚዋሰን በመሆኑ፣ የህዝባዊ አብዩቱ በሰላማዊ መንገድ ብቻ ካልተፈታ፣ የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት የኦሮሞና የአማራ ህዝብን እየገደለ መቀጠል ስለሌለበት ህዝቡ የጦር መሣሪያ እያነሳ በደም መላሽነት የአፀፋ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት፣የኢትዩጵያ ህዝብ ንብረት የሆኑ፣ተዋጊ የጦር አይሮፕላኖች፣ብረት ለበስ ታንኮች፣ሚሳኤሎች፣ላውንቸሮች፣የጦር ሠራዊት፣ የፖሊስ ሠራዊት፣ ወዘተ አሉት፡፡ሠራዊቱም ህዝቡን የማገልገልና የመጠበቅ፣ ሙያዊ ግዴታና ቃል-ኪዳን አለበት፡፡ህዝብን በጥይት መጨረስ ግን አይቻልም!!! አፈሙዙን በህወሓት የጦር አበጋዞችና ሹማምምቶች ላይ ያደርጋል፡፡

ለጎበዝ አለቆች

ህዝባዊ እንቢተኝነቱ ከአነስተኛ የግለሰብ ቤቶችን ከማቃጠል፣ ጠቃቅን ሱቆችንና የንግድ ቤቶችን ከማጋየት፣ እንዲሁም የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት፣ በትግራይ ብሄር ላይ ያነጣጠረ የዘር ፍጅት እያደረጉ ናቸው የሚለውን የፖሮፓጋንዳ ዘመቻ ለማክሽፍ ሁኔታዎችን ሊቀይሩ በማይችሉ ስራዎች ላይ የግለሰብ ንብረቶች ላይ ጉዳት ከማድረስ መቆጠብና ጭቁን ወታደሮችና ፖሊሶችን ጭምር በመቀስቀስ አፈሙዛቸውን ወደ የህወሓት/ኢህአዴግ የጦር አበጋዞች መንግስት፣እንዲያዞሩ የማድረግ ሥራና ደሞዝ የሚከፍላችሁ የኢትዩጵያ ህዝብ እንጂ ወያኔ አይደለም እያሉ በመቀስቀስ ማሳመን ያስፈልጋል፡፡ህዝባዊ እንቢተኝነቱ ከላይ በተገለፁት ወሳኝ የኢኮኖሚ ማእቀብ ውስጥ በመሳተፍ ወያኔን ጥይት መግዣ፣ደሞዝ መክፈያ፣ ቤንዚንና ናፍጣ መግዣ በማሳጣት ገቢውን በማሳጣት ማሽመድመድ ይቻላል፡፡

በዚህ ረገድ ቀጥለን በትግራይ ክልላዊ መንግስት እቅድን በተመለከተ ከቀረበው ሰነድ አንዳንድ መረጃዎች በሃገሪቱ ያስከተለውን ያልተመጣጠነ የኃብት ክፍፍልና የተዛባ የክልሎች እድገት እንድንቃኝና ይሄ በዘውግ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትለውን ኢፍትሃዊ ልማት ለማነፃፀር ይጠቅመናል፡፡ የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግስት፣ኢፈርት፣ሜቴክ፣ወዘተ የፓርቲው የንግድ ድርጅቶች፣ በትግራይ ህዝብ ስም የሌሎች ክልሎችን ኃብት በመዝረፍ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በመቆጣጠር፣ ለዘመናት የፖለቲካ በትረ ሥልጣኑን ለማስጠበቅ ላለፉት 25 አመታት፣ የኢትዩጵያ ህዝብን እየገደለ፣እያሰረ፣ እያሰደደ አንባገነናዊ ስርአቱን ማስቀጠል ችሎል፡፡ ዛሬ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የጋምቤላ፣ የደቡብ፣ የአፋር፣ የሱማሌ ወዘተ ህዝቦች፣የኢኮኖሚ ምዝበራው ይብቃ፣መሬቴን አትነካም፣ እህሌን አትጭንም፣ ወተቴን አታልብም፣ ወረወቄን አትዝቅም፣ ቡናዬን አትቀጥፍም፣አበባዬን አትቆርጥም፣ በማለት በህዝባዊ እንቢተኝነት የአልሞት ባይ ተጋዳይ ትግል በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ነው የትግራይ ምሁራን ምላሽ ሊሰጡበት የሚገባ የኢኮኖሚ ብዝበዛ በኢትዩጵያ ያስከተለው ህዝባዊ እንቢተኝነት ወደ የዘር ፍጅት(ጀኖሳይድ) ሳይሸጋገር ድርሻችሁን እንድትወጡና በተገኘው ማስረጃ ህዝብን ማሳወቅ ሙያዊ ግዴታችሁን፣በእውነት ለመመስከር የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግስት፣አደብ እንዲገዛ መምከር ይጠበቅባችኃል፡፡ በትግራይ ክልል ዕቅድ ከ2005 እስከ 2009 እኤአ የተከናወነውን፤የዕቅዱን አፈፃፀም መሠረት በመድረግ ለመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በመንደርደሪያነት የቀረበ ነው፡፡

## የትግራይ ክልላዊ መንግስት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (2010/11-2014/15)

### የህዝብ ብዛት

በ2007 እኤአ በወጣው የቤቶችና የህዝብ ቆጠራ ሪፖርት መሠረት 4,314,456 ሚሊዩን ህዝብ በትግራይ ውስጥ ሲኖር ከዚህም ውስጥ በፆታ ክፍፍል 49.2 % ወንድ፣ 50.2% ሴት ናቸው፡፡ የትግራይ ህዝብ ውስጥ 19.5 % በከተማ ሲኖሩ ቀሪዎ 80.5% በገጠራቶ ትግራይ እንደማንኛውም ኢትዩጵያዊ ዜጎች የሚኖሩ ናቸው፡፡ በትግራይ ህዝብ ቁጥር እድገት ከ2006 እኤአ 2.67 % በመቀነስ በ2007እኤአ 2.5 % ሆኖል፡፡

በትግራይ ክልላዊ መንግስት በ2001 የኢትዩጵያ አቆጣጠር፣ መንግስት ሰራተኞና የክልል፣የዞንና የወረዳ የተማረ የሰው ኃይል ፣የመንግስት ሠራተኖች ብዛት 61,246 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 33.8% ሴቶች ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ 27,626 መምህራን፣5,859 የጤና ኦፊሰርስ፣4,072 የግብርና ኤክስፐርቶች፣222 አቃቢ ህግ አዋቂዎች፣234 ዳኞች፣4,267 ፖሊሶች፣1,185 ሹማምንቶች ይገኙበታል፡፡

**የኢኮኖሚ እድገት Economic Development**

1}በውጪ ንግድ⁝የክልሉ ግብርና እድገት በአመዛኙ የግብርና ምርቶች ሲሆኑ በውጪ ንግድ ላይ ያተኮሩ ሰሊጥ፣ል ልዩ እህሎች፣ሙጫ፣ እጣን፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ወዘተ ናቸው፡፡ በ2006 እኤአ 51,776 ቶን ሠሊጥ ወደ ውጭ ተልኮ 50 ሚሊዩን ዶላር ገቢ ተገኝቶል፡፡ በ2008እኤአ 1.3 ሚሊዩን ኩንታል ሠሊጥ ተመርቶ 90,000 ቶን ሰሊጥ ወደ ውጭ ኤክስፖርት ተደርጎ በፖርት ሱዳን በኩል ለዓለም አቀፍ ገበያ ቀርቦ 121.5 ሚሊዩን ዶላር የውጪ ምንዛሪ ለክልሉ አስገኝቶል፡፡ *When we take sesame alone, in 2006 by exporting 51,776 tons, a total of 50 million dollar was earned and out of the 1.3 million quintals of sesame produced/ harvested in the production year of 2008, over 90,000 tons was exported to the international market through port Sudan and eventually over 121.5 million dollar foreign/hard currency was earned.*

2}ኢንቨስትመንት ፍሰት⁝በሌላ በኩል ባለፉት 13 አመታት ውስጥ ከ1992- 2005 እኤአ በክልሉ ውስጥ 822 ፕሮጀክቶች በ6.5 ቢሊዩን ብር ካፒታል ኢንቨስት አድርገዋል፡፡ ከ2006-2009 እኤአ በክልሉ ውስጥ 1389 ፕሮጀክቶች በ12.8 ቢሊዩን ብር መዋለ-ንዋይ አፍሰው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ፕሮጀክቶች ኢንቨስትመንት 92000 የክልሉ ዜጎች በመቅጠር የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡ በዚህ መሠረት ከ2002 እስከ 2005 እኤአ የግሉ ዘርፍ ባለኃብት ከ 20 በመቶ አመታዊ አማካኝ እድገት አስመዝግበዋል፡፡ በመቀጠልም ከ2006 እሰከ 2009 እኤአ 50 በመቶ አመታዊ አማካኝ እድገት አሳይተዋል፡፡

*On the other hand, in the last thirteen years /1992 –2005/ 822 projects with the capital of 6.5 billion birr were approved/ licensed and in the years 2006-2009 around 1389 projects with total capital of 12.8 billion birr were approved. These investment projects have created job opportunities for over 92,000 citizens. Therefore, the growth of private investment has grown from an average of 20% in the years 2002-2005 to the average annual growth of 50% in the years of 2006-2009 among the approved/ licensed investment projects, in the year 2002, 40.8 % have already started their production.*

3}የብድርና ቁጠባ አቅርቦት⁝በትግራይ ክልል ኢኮኖሚ እድገት ትልቁን ሚናና ድርሻ የሚጫወተው ለከተማና ገጠር ነዋሪዎች የሚመቻችላቸው የባንክ የብድርና ቁጠባ አገልግሎቶች እንደሆኑ ሰነዱ ይተቁማል፡፡ በዚህም መሠረት ከ2006 እስከ 2009 እኤአ ከሁለት ቢሊዩን ብር በላይ የብድር አቅርቦት ለገበሬዎች በምግብ እራሳቸውን እንዲችሉ ተመቻችቶላቸዋል፡፡ የደደቢት የጠቃቅንና አነስተኛ የብድር አቅርቦት ለገበሬዎች ብድር በማመቻቸት ትልቅ ሚና ተጫውቶል፡፡ *In our region, the credit/loan given in the rural as well as in the urban areas has played a great role in accelerating the economic development. In the years 2006-2009 over 2 billion birr credit was given to the farmers who were involved in the food security package and to those who were engaged in micro and small scale enterprises to purchase some facilities by the financial institutions such as Dedebit and other corporate enterprises.*

4}የንግድ እድገት⁝በትግራይ ክልል በ2005 እኤአ የነጋዴዎች ቁጥር ብዛት13,370 የነበረ ሲሆን በ2009 እኤአ 38,243 ከፍ ብሎ‌ል፡፡ በአለፉት አምስት አመታት ውስጥ 90,699 ነጋዴዎች የንግድ ፍቃድ ሲያወጡ ሀዚሁ ውስጥ የ32,304 አዲስ የንግድ ፍቃድ ያወጡ መሆናቸው ታውቆል፡፡

5}ስራ አጥነት⁝በ2003 እኤአ የጠቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ስር የተደራጁ ማህበራት ቁጥር 49,392 የነበረ ሲሆን በ2009 እኤአ 106,745 ከፍ ብሎ‌ል፡፡ በዚህም ምክንያት ከ2005 እስከ 2009 እኤአ በነዚህ የጠቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ማህበራቶች የብድር አቅርቦት ሽፋን 193,286 ሰዎች የስራ እድል አግኝተዋል፡፡ እንደ ማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ 2003 እኤአ ሪፖርት መሠረት⁝ በትግራይ ክልል ከተሞች ውስጥ የሚገኙ ስራ አጦች 28.8 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2009 እኤአ ወደ 19 በመቶ ዝቅ ማለት ችሎ‌ል፡፡

*In 2003 the number of the micro and small scale enterprises was 49,392 and in 2009 the number has grown into 106,745 and these enterprises were organized and strengthened. As a result, in the years 2005-2009, around 193,286 job opportunities have been created. According to the report of the central statistical agency, unemployment rate in the urban areas of the Tigray regional state in the year 2003 was 28.8 % of which 20.6 % were males and 36.2 % were females but this unemployment rate has decreased to 19.0 % (11.2% males and 16.2 % females) in the year 2009%.*

6}የግብር ገቢ አሰባሰብ ስርዓት⁝በክልሉ በ2006እኤአ 257.8 ሚሊዩን ብር የግብር ገቢ ሲሰባሰብ በ2009 እኤአ 633.3 ሚሊዩን ብር ገቢው ከፍ ብሎ‌ል፡፡ ከትግራይ ክልል አጠቃላይ በጀት የግብር ገቢ ድርሻ ከ 24.5% (2005እኤአ) ወደ 27.5% (2009እኤአ) ከፍ በማለት እድገት አሳይቶል፡፡ *In our region, evidences show*

*that the regional revenue collected every year has grown significantly. In 2006, a total of 257.8 million birr was collected and this amount of the regional revenue has grown into 633.3 million birr in the year 2009. When we see the regional revenue in relation to the regional total budget, it has grown from 24.5% in 2005 to 27.5 % in the year 2009.*

**የመሠረተ-ልማት እድገት Infrastructure development**

1} *መንገድ ሥራዎች*፤በክልሉ *መንገድ ሥራዎች* እድገትን በተመለከተ ከ2009 እኤአ በፊት ባሉ አመታቶች 1671 ኪሎ ሜትር ዋና *መንገዳች* ውስጥ 488 ኪ/ሜ አስፋልት *መንገድ*፣1357 ኪሎ ሜትር የገጠር *መንገድ*ና በአጠቃላይ 3028 ኪ/ሜ *መንገድ* በክልሉ *መንግስት*፣በፌዴራል *መንግስት*ና በለጋሽ ድርጅቶች ተሠርተዋል፡፡ በዚህም *መሠረት*፤በ2005 እኤአ የክልሉ *መንገዶች* ሽፋንና ትስስር 1000 $km^2$ ሽፋን ከ53 ወደ 56 ኪሎ ሜትር በ2009 እኤአ እድገት አሳይቶል፡፡ በ2005 እኤአ ከ1000 ህዝብ ብዛት ባለበት የ*መንገድ* ሽፋኑና ትስስር ከ0.41 ኪሎ ሜትር የነበረ ሲሆን በ2009እኤአ 0.64 ኪ/ሜ የ*መንገድ* ኔትወርክ ትስስር ከፍ ብሎል፡፡ በ2009 እኤአ በሃገሪቱ ደረጃ ያለው፤ የ*መንገድ* ኔትወርክ ትስስር 43 ኪሎ ሜትር በየ1000 $km^2$ ነው፡፡ እንዲሁም የ1000 ህዝብ ድርሻ 0.57 ኪሎ ሜትር ጋር ሲነፃፀር የትግራይ ክልል ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪ በከተማዎች ውስጥ 33 ኪ/ሜ አስፋልት *መንገድ*፣ 198.84 ኪ/ሜ የጠጠር *መንገድ*፣27.6 ኪ/ሜ ኮብል ስቶንና 62.87 ኪ/ሜ የፍሳሽና ቁሻሻ ማስወገጃ የመሠረተ ልማቶች ተከናውነዋል፡፡

*Based on this, in the years before 2009 around 1671 km main roads (of which 488 km is asphalt), 1357 km rural road and totally 3028 km road was constructed by the regional government, federal government and other donor organizations. Thus, when we see density network of our region in 1000 km2, it has grown from 53 in 2005 to 56 km in the year 2009 and in population number of 1000, the road coverage has increased from 0.41km which was in 2005 to 0.64km in 2009 especially the road which is still under construction is very important in importing commodities directly to our region within a very short period of time. In addition, in the urban areas 33kms asphalt 198.84kms gravel, 27.6 kms coble stone and 62.87 km drainage/sewerage are already constructed and are open to traffic.*

*‹In 2009, the density of road at national level was 43km in 1000 km2 and the share of 1000 people was 0.57 km but, in our region, the density was 56km in 1000km2 and 0.69km for 1000 people and hence we can say that our region is in a better situation. ›*

2} ቴሌኮምኒኬሽን ዘርፍ፤በቴሌኮምኒኬሽን ዘርፍ 226751 ደንበኞች የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ 64 በመቶ የስልክ አገልግሎት ሽፋን በክልሉ ተዳርሶል፡፡ በተመሳሳይ 153374 ደንበኞች የመሥመር ስልክ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ መሥመር አልባ ስልክ ተገልጋዩች 90 በመቶ ከፍ ብሎል፤ ይህ ማለትም አንድ ሰው መስመር አልባ ስልክ በ5 ኪሎ ሜትር ውስጥ አገልግሎት ማግኘት ይችላል፡፡ *On the other hand, an encouraging achievement has been registered in the expansion of telecommunications. Hence, 226,751 customers/ clients are able to use mobile phone and the mobile phone network covers 64% of the land. Similarly, over 153,374 customers are beneficiaries of the land line telephone and the coverage for wireless telephone is 90% which means one person can get a wireless telephone in every walk of 5 km.*

3} የመብራት አገልግሎት፤ በክልሉ 197 ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች የመብራት አገልግሎት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ሆነዎል፡፡ በአጠቃላይ 121953 አባወራዎችና እማወራዎች የኮረንቲ ፍጆታ ተዳርሰዋል፡፡ በዚህም የክልሉ የመብራት ኃይል ሽፋን 12 በመቶ ከአጠቃላይ ቤቶች ተዳርሶል፡፡ *As a result, 197 towns and rural centers are already benefited from the electrification program. In general, 121953 households have already got electric consumption counter and this means that the electrification covers 12 % of the total households.*

4} የውሃ አገልግሎት፤ የንፁህ ውሃ አቅርቦት በከተማ ክልል ውስጥ 50 በመቶ ወደ 72 በመቶ ሽፋን አግኝቶል፡፡ በገጠር አካባቢዎች ደግሞ ከ 41 በመቶ ወደ 60 በመቶ እንደደረሰ ሰነዱ ያሳያል፡፡*When we see the health problem in our region, evidences show that most of the health problems are caused due to lack of clean water. Thus, so as to solve this problem, the government has been engaged in upgrading the clean water supply both in the urban and in the rural areas and eventually the coverage of potable water in urban areas has grown from 50% to 72% and in the rural areas it has increased from 41% to 60%.*

5} የጤና አገልግሎት ሽፋን፤ በክልሉ ከ2005 እስከ 2009 እኤአ የጤና ማዕከል ቁጥር ብዛት ከ40 ወደ 200፤ሆስፒታል 14 ብዛቱ አልጨመረም፤ የጤና ኬላ ቁጥር ብዛት 611 የነበረ ሲሆን ቁጥሩ ቀንሶ 568 ሆኖል፡፡በአጠቃላይ በክልሉ የጤና አገልግሎት ሽፋን ከ75 በመተ ወደ 83 በመቶ አድጎል፡፡ የህፃናት ሞት ከአንድ ዓመት በታች ባሉ 104 ከአንድ ሽህ ህፃናት የነበረው 73 ከአንድ ሽህ ሕፃናቶች ሆኖል፡፡ እንዲሁም የእናቶች የወሊድ ግዜ ሞት ከ870 ከመቶ ሽህ ይሞቱ የነበረው 673 ከመቶ ሽህ እናቶች የእናቶች ሞት ቀንሶል፡፡

*Eventually, the coverage of health services has increased from 75 % to 83 % and the death of infants less than a year has fallen from 104/1000 to 67 /1000 and the death of children under the age of 5 years was reduced from 169/1000 to 73/1000. In the same way, the maternal mortality is reduced from 870/100000 to 673/100000 and the integrated family health is reached 75 % and among those who are involved in the integrated health package 70 % of them are beneficiaries of their own private toilets.*

6} የትምህርት አገልግሎት፤ በክልሉ በ2005እኤአ 1478 የመጀመሪያ ደረጃ፣59 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የነበሩ ሲሆን በ 2009 እኤአ 1978 የመጀመሪያና 110 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥራቸው በመደግ ተሠርተዋል። በዚህም መሠረት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር 99.77 በመቶ 102.8 በመቶ፤ ጁኒር ሰከንደሪ ተማሪዎች ቁጥር 38.7 በመቶ ወደ 50.2 በመቶ ክፍ ብሎል። *In 2005, there were 1478 primary and 59 secondary schools but in the year 2009 this number has grown to 1978 and 110 schools respectively. The gross enrollment rate in primary education has grown from 99.77 % in 2005 to 102.8 % in 2009 (103.4 % females and 102.1 % males) and in the junior secondary schools the enrollment rate has grown from 38.7 % to 50.2 % (50.7% males and 49.7% females). Similarly, the net enrollment rate in the elementary schools has increased from 86.77% in 2005 to 92.5% in the year 2009 (94.4 % females and 90.5% males).*

7} የቤቶች ልማት፤ በትግራይ ክልል በስትራቴጂክ ፕላኑ መሠረት 30115 ቤቶች ለመገንባት ከብሄራዊ ባንክ 1.197 ቢሊየን ብር ብድር ተገኝቶል። በቤት ልማት ፕሮጀክቱ በፈጠረላቸው የሥራ እድልም 490 ጠቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ማህበራቶች ተደራጅተው ለ5,799 አባሎቶቻቸው ቆሚ የስራ እድል ፈጥረዋል፣ እንዲሁም 5,895 ዜጎች ጊዜያዊ የስራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል። ለአምስት አማካሪ ድርጅቶች 2,000 ፕሮጀክቶችን እየተቆጣጠሩ እንዲያሰሩ የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል።

8)የግብርና ግብኣቶች አገልግሎት፤የትግራይ ክልል የአምስት አመቱ ስትራቴጂክ ፕላን 2005/6 እስከ 2008/9 ድረስ የእቅዱ አፈፃፀም በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት፣ የግብርና ዘርፍና የገጠር ልማት በክልሉ 1,023,246 ሄክታር መሬት ወደ 1,229,598 ሄክትር መሬት መታረሱን ሰነዱ ያመለክታል። በዚህም መሠረት በ2004/5 ምርት ወቅት 11.35 ሚሊዩን ምርት ተገኝቶል፣ በ2005/6 14.9፣ በ2006/7 17 ሚሊዩን በ 2008 እኤአ 16.4 ሚሊዩን፣በ2009 እኤአ 19.6 ሚሊዩን፣በ2010 34 ሚሊዩን ኩንታል እህል መመረቱ ተገልፆል። በግብርና ግብአት ረገድም በክልሉ ከ2005 እስከ 2009እኤአ 1,059,872 ኩንታል ማዳበሪያ፣ 676,808 ኩንታል ምርጥ ዘርና 1,242 ኩንታል ምርጥ የአትክልት ዘር ለገበሬዎች ተሰራጭቶል። የመስኖ ልማትን በተመለከተ በ2004እኤአ 15,045 ሄክታር መሬት ለምቶል። በ2005 እኤአ 18,200፣በ2006 እኤአ 38,180፣በ2007 እኤአ 37,462፣ በ2008እኤአ 40,845 ሄክታር መሬት እየለማ መጥቶል። በመስኖ ልማት የታቀፉ ገበሬዎች ብዛትም 159,295 ወደ 378,654 ቁጥሩ አድጎል።

8} የአይሮፕላን ማረፍያ፤ የትግራይ ክልላዊ መንግስት ሦስት ደረጃቸውን የጠበቁ የአይሮፕላን ማረፍያዎች በመቐሌ፣አክሱምና፣ሁመራ (የጎንደር መሬት ወደ ትግራይ በጉልበት የተጠቃለለ) *Tigray owns three standardized Air Ports that are located in Mekelle, Axum and Humera. The Air Transportation of the region then assists in increasing the number of visitors who come to visit the natural topography, cultural and historical heritages and other tourist attractions of the region. Moreover, it is believed that the air ports can also have positive impact in facilitating the regional investment.*

9} ኃይድሮ ፓወር ግድብ፤ በክልሉ የተገነባው የተከዜ ኃይድሮ ፓወር ግድብ በ1.5 ቢሊዩን ብር የግንባታ ወጪ 360 ኪሎዋት የኤሌትሪክ ኃይል እንዲያመነጭ ታቅዶ፤ እስካሁን 75 ኪሎዋት ብቻ እንደሚያመነጪ ይታወቃል። አሁን ምንም አያመነጭ።

10} የማዕድን ኃብት(Mineral resource)

በትግራይ ክልላዊ መንግስት የገንዘብና ፕላን ቢሮ በነደፈው የእድገትና ትራንስፎርሜድን ፕላን (2010/11-2014/15) በገፅ 17 መሠረት፤ ከ1999 እኤአ ጀምሮ፤በትግራይ ክልል አጠቃላይ፤የስነ-ምድር ካርታ ጥናት መሠረት፤በዓይነት፣ በሚሸፍነውና በመጠኑ የክልሉን የማዕድን ኃብቶች መለየት ተችሎል። እስካሁን የስነ-ምድር ካርታ ጥናት እንቅስቃሴ መረጃ መሠረት 24,780 ሜትር ስኮይር የስነ-ምድር ጥናት ተጠንቶና ተጠናቅሮ ሪፖረቱ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ነው። በትግራይ ክልል የስነ-ምድር ካርታ ጥናት ስብስብ መረጃ 46.2% ደርሶል፤እናም ክልሉ 850 ኪሎ ግራም ወርቅ በኢትዩጵያ ብሄራዊ ባንክ ተቀማጭ አድርጎል። በዚህም ረገድ፤ የተወሰኑ ድክመቶች ስላሉ አስፈላጊው ትኩረት ሊደረግላቸው ከሚገቡት መኃል፤ የሰለጠነ የሰው ኃይል ልማት፣ የመመርመሪያ መሣሪያዎችና የላብራቶሪ አገልግሎቶች ማሞላትና ሌሎቹም ነጥቦች ይጠቀሳሉ። በዚህ መሠረት 850 ኪሎ ግራም ወርቅ 850,000 ግራም ወርቅ ይሆናል ይሄን ለ29 ግራም (1 ወቄት ማለት ነው) ስናካክለው 29,310 ወቄት ወርቅ ይሆናል ይሄን በ1 ወቄት ዋጋ 1,218.80 ዶላር ስናባዛ 35,773,448 ሚሊዩን ዶላር ይሆናል በብር ስንቀይረው ደሞ በ20.34 ሲባዛ 726,768,548.7 የህወሃት ጦር አበጋዞች በብሄራዊ ባንክ አከማችተዋል ማለት ነው። ዝርዝሩን ከድረ-ገፁ ያንብቡ። ‹‹Since 1999, geological map survey has been conducted so as to identify the type, coverage and amount of mineral resources in our region. Up to now, the activities of collecting geological information from 24,780 meter square and consolidating reports have been finalized. The geological map coverage of our region has

reached 46.2% and around 850 kg gold is already deposited in the national bank of Ethiopia. In this regard, there were some limitations which need due attention such as fulfilling enough skilled manpower and inspecting equipments and laboratory services among others.›› (Tigray Regional State, Five Years 2010/11-2014/15, Growth & Transformation Plan, Bureau of Plan and Finance, September 2003 E.C, Mekelle, page 17)

Next Five Years (2010/11-2014/15) Regional GTP: Tigray Region Plan and Finance Bureau.

11} ኢዛና መዕድን ኃብት ኃ/የ/ግ/ማ (Ezana Mining)

ኢዛና ማዕድን ልማት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር (Ezana Mineral Development Private Limited Company (EFFORT በህወሃት/ ኢፈርት ባለቤትነት የተቆቆመ ካንፓኒ ሲሆን በትግራይ ክልል ውስጥ የተገኘውን 13 ቶን ወይም ፣13 000 ሽህ ኪሎ ግራም የወርቅ ማዕድን ለዓለም ዓቀፍ ጨረታ በማውጣት የካናዳዊያን የወርቅ ማዕድን ካንፖኒ ጋር ህወሃት/ኢፈርት በትግራይ ህዝብ ስም የሚዘረፊው የወርቅ ሃብት ነው፡፡ኢዛና ካንፓኒ 393.7 ሚሊዩን ብር የፕሮጀክት ወጪ 2017 ኪሎግራም ወርቅ በሁለት ዓመታት ውስጥ ለመማምረት አቅዶል፡፡በዚህ መሠረት 2017 ኪሎ ግራም ወርቅ 2,017,000 ግራም ወርቅ ይሆናል ይሄን ለ29 ግራም (1 ወቄት ማለት ነው) ስናካክለው 69,552 ወቄት ወርቅ ይሆናል ይሄን በ1 ወቄት ዋጋ 1218.80 ዶላር ስናባዛ 84,769,977.6 ሚሊዩን ዶላር ይሆናል በብር ስንቀይረው ደሞ በ20.34 ሲባዛ 1,724,221,344.384 ቢሊዩን ብር የህወሃት ጦር አበጋዞች በውጪ ሃገር ባንኮች ያከማቻሉ ማለት ነው፡፡

የሰነዱ ማጠቃለያ

የትግራይ ክልላዊ መንግስት እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (2010/11- 2014/15) የተቀመጠው ግብ የክልሉን እድገት 11 በመቶ በአማካይ በየአመቱ ማስቀጠል፡፡

- የኢኮኖሚ ዘርፍ እድገት በተመለከተ የግብርና ዘርፍ ካለበት ከ9.6 በመቶ እድገት  ወደ (ዝቅ ካለ 9.5 በመቶ፤ ከፍ ካለ14.9 በመቶ)፤
- ኢንደስትሪ ዘርፍ ካለበት 10.1 በመቶ እድገት ወደ (ዝቅ ካለ15.0 በመቶ፤ከፍ ካለ 19.0 በመቶ)፤
- አገልግሎት ዘርፍ ካለበት ከ11.6 በመቶ እድገት  ወደ (ዝቅ ካለ10.6 በመቶ፤ከፍ ካለ 12.8 በመቶ)
- ነፍስ ወከፍ ገቢ ካለበት 1900ብር ወደ (ዝቅ ካለ 2421ብር፣ ከፍ ካለ 2848 ብር) ወይም ካለበት 232 ዶላር (ዝቅ ካለ 295 ዶላር ከፍ ካለ 347ዶለር)፤
- የድህነት ቅነሳ አሁን ካለው 32.8 በመቶ ወደ (26.0 በመቶ እስከ 23.8 በመቶ)ዝቅ ማድረግ፤
- የሰራ አጥነት ችግርን መቀነስ ካለበት 19 በመቶ ወደ (15በመቶ እስከ 13 በመቶ)ዝቅ ማድረግ
- የግብርና ዘርፍ 38.7 በመቶ ለአማካኝ ብሄራዊ ምርት በአመት አስተዋፆኦ ወደ (37.1- 38.2 ) ማሳደግ፡፡
- የኢንድስትሪ ዘርፍ 19.4 በመቶ ለአማካኝ ብሄራዊ ምርት በአመት አስተዋፆኦ ወደ (21.2- 21.0 ) ማሳደግ፡፡
- የአገልግሎት ዘርፍ 41.9 በመቶ ለአማካኝ ብሄራዊ ምርት በአመት አስተዋፆኦ ወደ (41.7- 40.8 ) ማሳደግ፡፡
- በውጪ ንግድ፤በሚቀጥሉት አምስት አመታት ወደ ወጪ የሚላኩ የግብርናና ኢንደስትሪ ምርቶችንና ሽቀጣ ሽቀጦችን በመላክ 1.5 ቢሊየን ዶላር ገቢ ማግኘት፡፡

**The Presence of EFORT Plants :-**The EFORT plants which are found in Tigray region play a significant role in creating conducive atmosphere for investment, technological transformation, obtaining foreign currency, improving regional income and stabilizing the market. For the future, by strengthening their capacity the plants will underway the stated and other relevant roles. Therefore, the existence of these plants in the region is an asset as they foster different developmental activities.

የትግራይ ክልላዊ መንግስት እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (2015/16 - 2019/20) ሁለተኛው የአምስት አመት እቅድ መሠረት የተቀመጠው ውጥን ደግሞ በአጭሩ እንቃኛለን፡፡

1} ብረት መንገድ ባቡር ሀዲድ፤ከመቐለ - ታጁራ ወደብ በ3.2 ቢሊዩን ዶላር ለሚገነባው ባቡር መስመር የመሠረት ድንጋይ ተቀመጠ፡፡757 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት በሁለት ክፍል ተከፍሎ የሚካሄድ ነው፡፡ የመጀመሪው ከመቐለ እስከ ወልዲያ (ሃራ ገበያ) የሚገነባው 368 ኪሎ ሜትር የባቡር መሥመር በቻይና ኮሙኒኬሽን ኮንስትራክሽን ካምፓኒ (ሲሲሲሲ) የግንባታ ሥራውን ተረክቧል፡፡ ህ ግንባታ 1.6 ቢሊዩን ዶላር ሲሆን ከቻይና ኤግዚም ባንክ ብድር ተገኝቶል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ 389 ኪሎ ሜትር የባቡር ሃዲድ መሥመር በቱርክ ኩባንያ ያፒ ማርከንዚ ኮንስትራክሽን ካምፓኒ በ1.7 ቢሊዩን ዶላር የግንባታ ወጪ ለመስራት ታቅዶል፡፡ ብድሩ በቱርክ መንግስትና ከክሬዲት ስዊስ እንደተገኘ ተገልፆል፡፡ የባቡር መስመሩ ስሜን ኢትዩጵያን ከማዕከላዊ የአገሪቱ ክፍል የኢትዩጵያ ዋነኛ የወጪና ገቢ ንግድ በር ከሆነው ጂቡቲ ወደብ ያገናኛል፡፡ በአፋር ክልል የተገኘውን የፖታሽ ማዕድን ወደ ትግራይ ክልል በማጠቃለል ይህን የፖታሽና ሬድ ፖታሽ በማውጣት ከ250 እስከ 500 ሚሊዩን ዶላር የውጪ ምንዛሪ ለማግኘት እንደሆነ መረጃው ይገልፃል፡፡ አላና የፖታሽ ማዕድን ይዞታ 300 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን ፤ከዚህ ውስጥ 200 ካሬ ኪሎ ሜትር የሚሆነው ቦታ በፖታሽ ማዕድን የተሸፈነ መሆኑ በጥናት ጠረጋግጦል፡፡ አላና ፖታሽ በዳሎል 3.2 ቢሊዩን ቶን የፖታሽ ክምችት መኖሩን ትናቱ ቸምሮ አረጋግጦል፡፡ በዓለም በማዳበሪያ ምርት የሚታወቀው የእስራኤል ኬሚካል አይሲኤል በአፋር ክልል የፖታሽ ማዕድን ፍለጋ ላይ ለአመታት የተሠማራውን አላና ፖታሽ ኩባንያ መግዛቱ ታውቆል፡፡ የእስራኤል አይሲኤል ኩባንያ 16 በመቶ አክሲን የነበረው ሲሆን አሁን 84 በመቶ ጨምሮ ሙሉ በሙሉ ንብረቱ አድርጎታል፡፡ የእስራኤል አይሲኤል በአፋር ዳሎል ፖታሽ ልማት ፕሮጀክት ላይ አንድ ቢሊዩን ዶላር ኢንቨስት በማድረግ ለ3000 ሠራተኞች የስራ እድል ይፈጥራል ተብሎ ይገመታል፡፡ በኣለም አቀፍ ገበያ በፖታሽ ምርት በብዛት በማምረት ሩሲያና ቤላሩስ ይታወቃሉ፡፡ የአንድ ቶን ፖታሽ ዋጋ 570 ዶላር የነበረ ሲሆን ዋጋው በመቀነስ አሁን 280 ዶላር በመሸጥ ላይ ይገኛል፡፡

2} የመቐለ ኢንደስትሪ ፓርክ ግንባታ በ500 ሄክታር መሬት ላይ የሚገነባ ሲሆን፤በፓርኩ የጨርቃጨርቅ ፣ቆዳና የቆዳ ውጤቶች እንዲሁም ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ፋብሪካዎች ካትታል፡፡

- ዱላል ብራዘርስ የተሰኘ የባንግላዲሽ ኩባንያ በመቐለ የኢንደስትሪ ዞን በ 76 ሄክታር መሬት በነፃ ተሰጥቶት 42 ሚሊዩን ዶላር ወጪ ዘመናዊ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ይገነባል፡፡
- በ400 ሚሊዩን ብር የተገነባው የሞሐ ለስላሳ መጠጦች ፋብሪካ ይገኛል፡፡
- የጣሊያን ኩባንያ ካልዚዶኒያ የገነባው የጂንስ ስፊት ፋብሪካ የጋርመንት ፋብሪካዎች በመገንባት ላይ ናቸው፡፡
- ግሪን ካፌ አግሮ ኢንደስትሪ ቢራ ፋብሪካ ለመገንባት 50 ሄክታር መሬት ተረክቦል፡፡

የትግራይ ክልላዊ መንግስት እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (2010/11- 2014/15) የተቀመጠው

3} የራያ ዩኒቨርሲቲ በትግራይ ደቡባዊ ዞን ማይጨው ከተማ በ200 ሄክታር መሬት ላይ በሁለተኛው የእድረትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደሚገነባ በሕወሃት 40ኛ ዓመት በዓል ላይ መሠረት ድንጋይ ተቀምጦል፡፡

4} የራያ ቢራ ፋብሪካ በማይጨው ከተማ በ150000 ስኮየር ሜትር ላይ የተገነባ ሲሆን፤ የግንባታው ወጭ 1.5 ቢሊዩን ብር ነው፡፡ራያ ቢራ ፋብሪካ ከኢትዩጵያ ንግድ ባንክ 910 ሚሊዩን ብር ብድር እንዳገኘ ይታወቃል፡፡ ራያ ቢራ አክሲዩን ማኅበር፣የፋብሪካው የማምረት አቅሙ 710 ሽህ ሄክቶ ሊትር ነው፡፡
*ለዚህ ነው ህዝባዊ ወያነ ሃርነት ትግራይ/ ወያኔ እንደ ማጭድ .....ወገቧ ጎባጣ ፤አገሩን ሁሉ ቆምጣ ቆምጣ!!! የተባለችው በዘውጌ ፖለቲካ የኢትዩጵያን ህዝብ ለሃያ አራት አመታት ስላባላው ነው!!!*

**Part I-1. Performance evaluation of the previous strategic plan /2006 -2010/**

**1.1 Macro economic conditions of the region**

The macro-economy situation of the region was evaluated based on some indicators like Regional Gross Domestic Product, the share of different economic sectors and the per-capita income among others. It was planned in the previous strategic plan (2005/06 -2009/10) to register an average growth rate of 10% annually. However, there was also a concerted effort to record above this average growth rate. Accordingly, due to the concerted effort, up to 2010, an average of 11 % growth was registered every year. Thus, as compared to the growth rate achieved in 2002-2004 which was 10.01 %, there is a difference of 0.99 %. When we see the average growth rate of sectors in the previous strategic plan, agriculture has been grown by 9.5%, industry by 9.5%, services by 13.2% respectively. For more information it is possible to see in table one below.

**Table 1: Regional GDP growth rate by economic sectors (2005/06- 2009/10)**

| No. | Description | Year | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2005/06 | 2006/07 | 2007/08 | 2008/09 | 2009/10 | Average |
| 1 | Total Regional GDP | 11.2 | 11.3 | 11.8 | 10.2 | 10.5 | 11.0 |
| 2 | Agriculture sector | 9.6 | 9.2 | 11.4 | 7.9 | 9.6 | 9.5 |
| 3 | Industry sector | 10.0 | 9.5 | 9.0 | 9.4 | 10.1 | 9.5 |
| 4 | Services sector | 14.0 | 14.4 | 13.7 | 13.0 | 11.6 | |

Source: Bureau of planning and Finance.

Out of the gross regional income(GDP) registered in the past strategic plan, the share of agriculture reduced to 38.7% in 2009/10 from what it had been at 40.9% in 2005/06 while that of industry reduced from 20.4% to 19.4% in the same period.. However, unlike the agricultural and industrial sectors, the share of services has shown a remarkable growth from 38.7 % to 41.9 % in the period under consideration same years. Reference is made in the table-2 below 3

**Table 2: Sectoral share to Regional GDP (in percentage) (2005/06 -2009/10)**

| No. | Sector | Year | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2005/06 | 2006/07 | 2007/08 | 2008/09 | 2009/10 | Average |
| 1 | Agriculture | 40.9 | 40.1 | 39.9 | 39.1 | 38.7 | 39.4 |
| 2 | Industry | 20.4 | 20.1 | 19.6 | 19.4 | 19.4 | 19.6 |
| 3 | Services | 38.7 | 39.8 | 40.5 | 41.5 | 41.9 | 41.0 |
| | Total | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

Source: Bureau of planning and Finance

This remarkable economic development was realized because of the significant growth in agricultural production and productivity; industry such as the expansion of mining, trade, construction, transport, financial institutions and the expansion of other infrastructures. The per capita income was found by dividing the overall RGDP to the then total population number.

**ተጨባጭ የነፍስ ወከፍ ገቢ**(the real per capita income)

**የትግራይ ክልል ተጨባጭ የነፍስ ወከፍ ገቢ፡-**

**በትግራይ ክልል ከ2005/06እኤአ የዜጎች ተጨባጭ የነፍስ ወከፍ ገቢ 1378 ብር ወይም 168 ዩኤስ ዶላር የነበረ ሲሆን በ2009/10 እኤአ 1900 ብር ወይም 232 ዩኤስ ዶላር መድረሱን ለዚህም እድገት ሠሊጥ ወደ ውጪ በመላክ ከፍተኛ ገቢ በፖርት ሱዳን በኩል ከ50 ሚሊዩን እስከ 121.5 ሚሊዩን ዶላር በማግኘታቸው እንደሆነ የክልሉ ሰነድ ያትታል፡፡**Thus, the real per capita income has grown from 1378 birr (168 USD) in 2005/06 to 1900 birr (232 USD) in 2009/10.There are some agricultural products which significantly contribute to the economic development of our region and are very important export items such as sesame and other cereals, gum and gum Arabica, leather and leather products, hides etc. When we take sesame alone, in 2006 by exporting 51,776 tons, a total of 50 million dollar was earned and out of the 1.3 million quintals of sesame produced/ harvested in the production year of 2008, over 90,000 tons was exported to the international market through port Sudan and eventually over 121.5 million dollar foreign/hard currency was earned. Therefore, this encouraging result indicates the possibility of increasing the contribution of such agricultural products to the economic development of our region if an integrated and intensified effort is made to increase the quality, quantity and competitiveness of these kinds of export of agricultural products.

**በትግራይ ክልል ከ1992 እስከ 2005እኤአ 822 ፕሮጀክቶች በ6.5 ቢሊዩን ብር ካፒታል ያላቸው የስራ ፍቃድ አግኝተው ነበር፡፡ በተመሳሳይ በ2006 እስከ 2009 እኤአ 1389 ፕሮጀክቶች በ12.8 ቢሊዩን ብር ካፒታል ያላቸው የስራ ፍቃድ አግኝተው ነበር፡፡ በትግራይ ክልል ተደረገው ይህ የኢንቨስትመንት ለ92000 ዜጎች የስራ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡** On the other hand, in the last thirteen years /1992 –2005/ 822 projects with the capital of 6.5 billion birr were approved/ licensed and in the years 2006-2009 around 1389 projects with total capital of 12.8 billion birr were approved. These investment projects have created job opportunities for over 92,000 citizens. Therefore, the growth of private investment has grown from an average of 20% in the years 2002-2005 to the average annual growth of 50% in the years of 2006-2009 among the approved/ licensed investment projects, in the year 2002, 40.8 % have already started their production.

**በትግራይ ክልል ከ2006 እስከ 2009እኤአ የደደቢት የማይክሮ ፋይናንስ/የብድርና ቁጠባ አገልግሎት 2 ቢሊዩን ብር ለደሃ ገበሬዎች ብድር አመቻችቶላቸው ተጠቃሚ አድርጎቸዋል፡፡**In our region, the credit/loan given in the rural as well as in the urban areas has played a great role in accelerating the economic development. In the years 2006-2009 over 2 billion birr credit was given to the farmers who were involved in the food security package and to those who were engaged in micro and small scale enterprises to purchase some facilities by the financial institutions such as Dedebit and other corporate enterprises. This kind of financial support is believed to have a great contribution in supporting the farmers and the micro and small scale enterprises that have financial constraints.

የትግራይ ክልል የገቢዎች ቢሮ ከ2006እኤአ 257.8 ሚሊዩን ብር ግብር አሰባስቧል በተመሳሳይ በ2009እኤአ 633.3 ሚሊዩን ብር የግብር ገቢ ሰብስቦል። የክልሉ ባጀትም ማደጉን ገልፀዎል። In our region, evidences show that the regional revenue collected every year has grown significantly. In 2006, a total of 257.8 million birr was collected and this amount of the regional revenue has grown into 633.3 million birr in the year 2009. When we see the regional revenue in relation to the regional total budget, it has grown from 24.5% in 2005 to 27.5 % in the year 2009 and in relation to the recurrent budget of our region; it has increased from 30.1% in 2005 to 43.2 % in 2009. When we compare the share of the region's overall revenue to RGDP in the same period, it has grown from 3.5 % in 2005 to 7.2 % in 2009. Of the total regional revenue collected in 2005-2009, the share of direct tax has grown from 80.2% to 82.0%, and the share of capital revenue from 0.4% to 2.5% but the share of indirect tax has decreased from 19.4 % to 15.5 %. Even though, the amount of the indirect tax collected every year was increasing, the growth was not as such significant.

## ሰበር የሃገር ውስጥ ዜና

1} በአዲስዘመን ጋዜጣ፣ ነሐሴ 19 ቀን 2008ዓ/ም (የሜ/ጄኔራል ኃየሎም አርአያ አውሮፕላን ማረፍያ ግንባታ በጥር ወር ይጠናቀቃል ተባለ) ሽሬ በሜጀር ጄኔራል ኃየሎም አርአያ ስም የተሰየመውና በ417 ሚሊዩን ብር በጀት እየተገነባ ያለው የሽሬ እንደሥላሴ ከተማ አውሮፕላን ማረፍያ የኮንክሪት አስፓልት ንጣፍ ግንባታ በመጭው ጥር ወር የሚጠናቀቅ መሆኑ ተገለፀ። የካቲት 2007 ዓ/ም ላይ የተጀመረው የአውሮፕላን ማረፍያ ግንባታ 2 ነጥብ 7 ኪሎሜትር ርዝመትና160 ሜትር ወርድ ማኮብኮቢያ ያለው ነው። ዲዛይኑ በቦይንግ ስታንደርድ 215 ሜትር ቁመትና 130 ሜትር ወርድ ያለው አውሮፕላኖች የሚጭኑበት ቦታ/ታክሲ ዌይ/ ያለውና ሁለት ቦይንግ 777 አውሮፕላኖችን ማስተናገድ እንደሚችል ተገልጾል።

2} በሪፖርትር ጋዜጣ፣ሰኔ 29 ቀን 2008ዓ/ም (ፔጆና መስፍን ኢንጂነሪንግ በውቅሮ መገጣጠሚያ ፋብሪካ አዋቅረዋል) በሚል ርዕስ በትግራይ ክልል ከመቐለ 40 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ውቅሮ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የመስፍን ኢንጂነሪንግ የተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ ፋብሪካ አማካይነት የሚገጣጠሙት  አውቶሞቢሎች ሦስት ዓይነት ሞዴሎች ናቸው። ከአንድ ቢሊዩን  ብር በላይ ወጪ ይጠይቃል የተባለው ግዙፍ የተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ በ50 ሄክታር መሬት ቦታ ላይ ግንባታው እንደሚያርፍና፣ በዓመት እስከ አንድ ሽህ ተሽከርካሪዎች ለገበያ ማቅረብ የሚችልበት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ታውቆል። መስፍን ኢንጂነሪንግ ፣ከጂሊና ከፔጆ የቤት አውቶሞቢሎች በተጨማሪ ከታዋቂው የጀርመን ኤመኤኤን ኩባንያ ጋር በቅርብ ባደረገው ስምምነት መሠረት ኤምኤኤን ከባድ ተሽከርካራች ገጣጥሞ ለገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛል። 250 ተሽከርካሪዎችን ገጣጥሞ ለደንበኞች ማስረቡን ተገልፆል። ከአራቱ መስፍን ኢንጂነሪንግ ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች የቤትና የከባድ ተሽከርካሪዎችን ከመገጣጠም ባሻገር፣ከህንድ ኩባንያ ጋር በመሆን ትራክተር ገጣጥሞ ለገበያ በማቅረብ ላይ እንደሚገኝ ታውቆል።  መስፍን ኢንጂነሪንግ ከአንድ ሚሊዩን ብር ባነሰ ካፒታል የተቆቆመ ኩባንያ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ የሚያንቀሳቅሰው ካፒታል ከ25 ሚሊዩን ዶላር በላይ (548 750 000 ሚሊዩን ብር) ካፒታል ያለው መሆኑን የኢፈርት ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይዘሮ አዜብ መስፍንና ዋና ስራ አስኪያጁ አቶ ሃብተ ሃዱሽ ገልፀዋል።

3} በሪፖርትር ጋዜጣ፣ቅፅ 21 ቁጥር 1695 (መሶቦ ሲሚንቶ ለ200 ተሽከርካሪዎች ከ800 ሚሊዩን ብር በላይ በማውጣት ከመስፍን ኢንጅነሪንግ ገዛ) መስፍን ኢንጂነሪንግ ፣የጀርመን ኤመኤኤን ኩባንያ ጋር በቅርብ ባደረገው ስምምነት መሠረት ኤምኤኤን (ማን)ከባድ ተሽከርካራች ገጣጥሞ ለገበያ በማቅረብ ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት 200 ተሽከርካሪዎችን ከ40 እስከ 50 ቶን የመጫን አቅም ያላቸው ከባድ መኪኖች ገጣጥሞ ለመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ በ800 ሚሊዩን ብር ሸጦል። መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ከመሃል አገር በ800 ኪሎ ሜትር ገደማ ያለውን ርቀትና የገበያ የበላይነታ ለማጥበብ በእነዚህ ተሽከርካሪዎች አማካይነት ምርቶቹን ወደ መሃል ገበያ ለማድረስ መነሳቱን የመሶቦ ሲሚንቶ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ክብረዓብ ተወልደ አስታውቀዋል። የማምረት አቅሙ 2.3 ሚሊዩን ቶን በዓመት ወይም በቀን 8000 ሽህ ቶን ሲሆን በአሁኑ ወቅት 1.97 ሚሊዩን ቶን የማምረት አቅም ላይ ደርሶል። ሆኖም ከመሃል ሃገር በ800 ኪ/ሜ ርቆ መገነቱ በዋጋ አካያ ተወዳዳሪነቱ ላይ ተፅዖኖ ስለሚያሳድርና አካባቢ ላይ የሚደርሰውን የብክለት ጫናን ለመቀነስም ወጪ ቆጣቢ አሠራሮችን መተግበር እንደጀመረ አስታውቆል።  ፋብሪካው ባለፈው አመት ከ330 ሚሊዩን ብር በላይ ማትረፉንና በሲሚንቶ ኢንዱሰትሪው ውስጥ የ24 በመቶ የገበያ ድርሻ መያዙ ተገልፆል። መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ውጤት የተገነቡ በሃገሪቱ 23 ዩኒቨርሲቲዎችን ጨምሮ፣ ታላቁ የህዳሴ ግድብ፣አሼጎዳ የንፋስ ሃይል

ማመንጫ፣ ግልገልጊቤ አንድ፣ሁለትና ሦስት ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች፣የአፍሪካ ህብረት ዋና መሥሪያ ቤት፣ አዋሽ ድልድይና የህዳሴው ድልድይን ጨምሮ በርካታ ፕሮጀክቶች በመሶቦ ሲሚንቶ የተገነቡ ናቸው፡፡መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣እነዚህን ሁሉ  ፕሮጀክቶች ስራ ያገኘው በጨረታ ነው ወይስ በህወኃት የጦር አበጋዞች መንግስት ትዕዛዝ!!! ፋብሪካው 800 ኪ/ሜ መንገድ የነዳጅ ዋጋው በሲሚንቶ ዋጋ ላይ ተጨምሮ ከሌሎች ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ጋር በገበያ ዋጋ ይስተካከላል ማለት ዘበት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በሃገሪቱ የሚሰሩ ከላይ የተጠቀሱት ፕሮጀክቶች የግንባታ ወጪ በጣም ከፍ ሊል እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ አስር ግዜ በላይ ከስሮ የተነሳው የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣የተለያዩ መንግስታዊ ፕሮጀክቶች ያለ አንዳች ጨረታ እየተሰጡት እንደ እባብ መሬት ልሶ ተነሳ ነው የሚሉን፡፡ ምን ዓይነት ጠባብነት ነው በሃገር ኃብት መጫወት በዚች ደሃ ሃገር በብድር የተገነቡት ፕሮጀክቶች የነገው ትውልድ እዳ፣ የህወኃት የፓርቲ ንግድ ድርጅቶች ትርፋማነት መለኪያ መሆኑ ያስተዛዝባል፡፡
መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣ የኃይል አጠቃቀሙን ወጪ ቆጣቢ ከማድረግ ባሻገር ብክለትን እንዲቀንስ የሚያስችል ባዩማስን (ከሠሊጥ አገዳ ከጎንደርና ፕሮሶፒስ ጁሊፍሎራ የተባለ አርም በአፋርና ሶማሌ ክልል የሚገኝ አረም ነው) ተጠቅሞ ኃይል የሚያመነጭ ቴክኖሎጂ ሥራ  ላይ እየሰራ እንደሚገኝና ለቴክኖሎጂው ከመቶ ሚሊዩን ብር በላይ አውሎል፡፡ ድንቅ ነው!!!

4} በሪፖርተር ጋዜጣ፣ግንቦት 21ቀን 2008ዓ/ም (አገር በቀል ኮንትራክተሮች የነገሡበት የ5.6 ቢሊዩን ብር የመንገድ ግንባታ ስምምነቶች) በሚል ርዕስ የቀረበ ዘገባ መሰረት የኢትዩጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አርዓያ ግርማይ ጋር ሰባት የመንገድ ፕሮጀክቶች ኮንትራክተሮች ተፈራርመዋል፡፡

- ሱር ኮንስትራክሽን፡-የኢፈርት ድርጅት ሲሆን፣ የሁለቱን የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ጨረታ አሸናፊ ሲሆን  ስራ አስኪያጁ አቶ ታደሰ የማነ ሱር ኮንስትራክሽን ከሰባቱ ፕሮጀክቶች ሁለቱን ከ3.3 ቢሊዩን ብር በላይ ያገኘው በአማራ ክልል ከሶሮቃ-አብረሃጂራ-አብደራፊ(92 ኪ/ሜ በ1.43 ቢሊዩን ብር) እና ከአይከል-ዘ-ፋን-አንገርብ(69 ኪ/ሜ በ1.95 ቢሊዩን ብር) ድረስ ያለውን መንገድ ለመገንባት ነው፡፡
- የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ፣በአማራ ክልል ውስት ሚያልፈውን የበለስ-መካነ ብርሃን 39ኪ/ሜ መንገድ(1.01ቢሊዩን ብር)ና በአፋር ክልል የሚገነባውን የአዋሽ ሚሌ(ኮንትራት አራት)74 ኪ/ሜ (በ381.8 ሚሊዩን ብር) ያለውን መንገድ ለመገንባት ነው፡፡
- ሱር ኮንስትራክሽንና የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግስት የአንበሳውን ድርሻ 4.691800000 ቢሊዩን ብር ተቀራምተዋል፡፡ ሃገር በቀል ነው ክልል በቀል!!! የማንን ክልል መንገድ ለመስራት ጠባቦች ገንቢ ሆነው ለመዝረፍ በጨረታ ስም አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ!!! ትንሽ አታፍሩም፡፡ ሌላው ክልል ምንም የተማረ ባለሙያ መንገድ ግንባታ ኮንትራክተሮች የሉትም ማለት ነው!!!
- ቀሪዎቹ የኢትዩጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከአዋሽ-ሚሌ (ኮንትራት ሦስት) 75 ኪ/ሜ በ440 ሚሊዩን ብር፣ማርካን ትሬዲንግ ከአዲስ አበባ-ሞጆ-መቂ 131ኪ/ሜ መንገድ ጥገና በ 210.31 ሚሊዩን ብርና ዩናታን አብይ ጠቅላላ ተቆራጭ ደግሞ የመቂ-ሻሸመኔ-ሃዋሳ መንገድ 146 ኪ/ሜ መንገድ በ 197.1 ሚሊን ብር ለመገንባት ኮንትራት ፈርመዋል፡፡

የትግራይ ምሁራን ሊገነዘቡት የሚገባ  በኢትዩጵያ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ዋነኛ  ኃብቶች በየትኞቹ ክልሎች እንደሚገኙ  ህወኃት/ኢህአዴግ ካሰራጨው የዲያስፖራ ድረ-ገፅ በመረዳት የትግራይ ህዝብ  ህዝባዊ እንቢተኝነቱ ትግል እንዲቀላቀል የማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነት አለባችሁ!!!

የትግራይ ህዝብ ኃብትና መልክአ ምድር

| ትግራይ | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | cattle | 2.7 million | 7% |
| | sheep | 72,640 | 0.42% |
| | goats | 208,970 | 1.61% |
| | horses | 1,200 | 0.1% |
| | mules | 9,190 | 6.24% |
| | asses | 386,600 | 15.43% |
| | camels | 32,650 | 7.15% |
| | poultry | 3.1 million | 10.3% |
| | beehives | 20,480 | 0.47% |

The CSA estimated in 2005 that farmers in Tigray had a total of 2,713,750 cattle (representing 7.0% of Ethiopia's total cattle), 72,640 sheep (0.42%), 208,970 goats (1.61%), 1,200 horses (less than 0.1%), 9,190 mules (6.24%), 386,600 asses (15.43%), 32,650 camels (7.15%), 3,180,240 poultry of all species (10.3%), and 20,480 beehives (0.47%).[9]

- **MAJOR ECONOMIC ACTIVITIES**

About 83% of the population are farmers. Teff, wheat, and barely are the main crops. Other agricultural products include beans, lentils, onions, and potatoes. Irrigation and terrace

farming are used on the steep slopes. The region is also known for its export items of cotton, incense, sesame and minerals. 1.5 million hectares of land in the region is cultivable, of which one million hectares is being cultivated, while 420,877 hectares of land is terraced. Handicraft (gold smith, painting and wood sculptures) is another area of activity observed in the historic cities of the state.

- **MINERALS**

  Tigray is one of the richest areas in Ethiopia in mineral resources. Some of the explored metallic minerals of the state include gold, copper, iron ore, zinc, lead and nickel. Asbestos, Silica sand, Kaolin, graphite, gypsum gemstone, marble, granite slate, limestone and dolomite are among the non-metallic minerals.

- **INVESTMENT**

  The state of Tigray has created favourable conditions and incentives in order to attract investors. So far, until the beginning of 1998, there were 361 projects with a capital of 4 billion Ethiopian Birr. These projects focus mainly on agriculture, industry, hotel and tourism, social services, mining, construction and transport. About 200,138 persons will benefit from the job opportunity created by these projects. The state also has large farming areas suitable for the production of cash crops such as cotton and different kinds of oilseeds.

## የኢኮኖሚ መርማሪ ኮሚሲዩን በአስቸኳይ ይቋቋም!!!

በኢትዩጵያ የተቀሰቀሰው ህዝባዊ እንቢተኝነት የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግስት መጣሉ አይቀሬ ነው፡፡ ህወኃት ህዝባዊ አብዩቱን ሃዲድ ለማሳት ህዝቡን በእርስ በርስ የዘር ፍጅት ለማጨራረስ በተለይ የትግራይን ህዝብ ላይ የኦሮሞና የአማራ ዘሮች እንደተነሱበት አድርጎ የፕሮፓጋንዳ መርዙን በመርጨት ላይ ይገኛል፡፡ ህዝባዊ እንቢተኝነት  በህወሓት/ኢህአዴግ የፓርቲ ንብረቶችን በማውደም ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም ህወሓት በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ አድርጎ መለፈፉና በሚቀጥሉትም  ግዜቶች የህወሓት የደህንነት ሰዎች እራሳቸው በትግራይ ባለኃብቶች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድ የዘር ፍጅት (ጀኖሳይድ) በትግራይ ሰዎች  ላይ ተካሄደ ለማለት በማሴር ላይ ይገኛሉ፡፡ አብሮ የኖረውን የትግራይ ህዝብ ከተለያዩ ክልሎች በማውጣት ላይ የሚገኘው ለዚህ ነው፡፡ ህዝባዊ እንቢተኝነት በቀጣይነት የኢኮኖሚ መርማሪ ኮሚሲዩን በየክልሉ በአስቸኳይ በማቋቋም የህወሓት/ኢህአዴግ የፓርቲና የድርጅት የንግድ ድርጅቶችን፣ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሙስና የተሸጡ ከ360 በላይ የሆኑ የመንግስት ድርጅቶችን፣ የመንግስት የነበሩ የእርሻ በተለይ የቡና የእርሻ መሬቶችን(በተለይ የከተማና የገጠር የመሬት ቅርምቶችንና የሪል ስቴት ባለኃብቶችን ንብረት የሚመረምር) ፣የኮንዶሚኒየምና የከተማ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን የገነቡ ባለሃብቶችን የገቢ ምንጫቸውን የሚያጣራ፣ በሙስና በሊዝ የተሸጡ የከተማና የገጠር መሬቶችን፣ ፋብሪካዎችን፣ የንግድ የአገልግሎት ሱቆችን፣ በአጠቃላይ በ**ኢትዩጵያ ኢኮኖሚ፤ የፌዴራል፣ክልል መንግስታዊ ኢንተርፕራይዞች፣ የኢፈርት፣ጥረት፣ዲንሾ፣ወንዶ፣ሜቴክና ሜድሮክ የቢዝነስ ሞኖፖለ**ዎችን ሃብትና ንብረት አጣርቶ  የሚያጠና የኢኮኖሚ መርማሪ ኮሚሲዩን በአስቸኳይ ማቋቋምና ንብረቶቹን መውረስና የህዝብ ሓብት ማድረግ አርቆ አስተዋይነት ነው!!!

**የኢትዩጵያ ህዝብ ህወሃት/ኢህአዲግ በክልሎች ከፋፍሎት የአንዱ ክልል ህዝብ፤ ሌላውን ህዝብ ከክልሌ ውጣ ከሚባባል ይሄን እነዚህን የህዝብ ሓብቶች በህግ፣ በማስረጃ አቅርቦ በሙስና በጎቦ ወዘተ የተገኙ ሓብቶችን ማስመለስ ይቻላል፡፡  ህዝባዊ እንቢተኝነት በየክልሉ ትልልቅ የሃገሪቱን ኃብቶች የሚያጠና ሚስጢራዊ ቡድን በማቆቆም ንብረቶቹን ሳናወድም የህዝብ ሃብት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህም እንደ ምሳሌ የምናቀርበው በኢትዩጵያ  የወርቅ ማዕድን ኃብትን ለማስመለስና ለኢትዬጵያ ህዝብ ጥቅም የሚውልበትን መንገድ ለመፈለግ የተሻለ አማራጭ አድርገን ያቀረብነው ጥናት የሃገሪቱን ህዝብ ከእርስ በእርስ ጦርነት በተለይ ከዘር ፍጅት (ጀኖሳይድ በአለም አቀፍ ህግ ህወሓት ይጠየቃል!!!)፣ከርሃብ ፣ከስደት ህዝባችንንና ሃገራችንን መጠበቅ፣በሰከነ ህሊና እያሰብን የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግስት ማስወገድ ታሪካዊ  ኃላፊነታችን ነው፡፡ የትግራይም ህዝብ ከኢትዩጵያዊያን ወገኖችህ ጎን ቆመህ ህወሓትን በህዝባዊ አመፅ ለመደምሰስ ታሪካዊ ሃላፊነትህን ተወጣ፡፡ ለኢፈርት የኢዛና የወርቅ ማዕድን ሰጥቶና ለሼክ መሃመድ የለገደንቢ የወርቅ ማዕድን ሰጥቶ አንዱን ደሃ ገበሬ ክልሌን ለቀህ ውጣ አትውጣ ማለት ‹‹አህያውን ፈርቶ ዳውላውን!›› ወይም ድመት እንዳለችው ‹‹ ምን ቢታለብ በገሌ!›› አይሆንምን፡፡ እኛ በብሄር ብሔረሰብ፤በሃይማኖት ወዘተ፤አንዱ ከአንዱ ሲጣላ ወርቁ ተዝቆ ያልቃል፡፡ ‹‹የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ!!!›› ይላሉ ቅድመ አያቶቻችን ሲተርቱ፡፡ ልብ ያለው ልብ**

**ይበል!!! ህዝባዊ ክብር ለተሠው ሰማዕታት!!! በሃገር አቀፍ ደረጃ ቤት ውስጥ ቁጭ የማለት አድማ ይጠራ!!!**

ለአንባገነን መንግስት፣ ህዝብን ላልወከለ፣
አይገዛም ህዝቡ፣ ሳለ እየታገለ!!!
አይገዛም! አይገዛም!! አይገዛም!!!
ለቻይናዎች ጭፍራ፣ ለሱዳን ቡችላ፣
አይገዛም ህዝቡ፣ ከዛሬ በኃላ፡፡
አይገዛም! አይገዛም!! አይገዛም!!!
በፋሽስቱ ወያኔ፣የተገደላችሁ
በሹንባሹ አጋዚ፣ የተረሸናችሁ
አትረሱም ፍፁም ተከታዬች አሉ
አይገዛም! አይገዛም!! አይገዛም!!!
ወንድሙን ሲገለው፣ ወንድሙን ካልከፋው
ኦሮሞን ሲገሉት፣ አማራው ካልከፋው
ሱሪውን አምጡለት፣ ደሙ እንዲከረፋው
አይገዛም! አይገዛም!! አይገዛም!!!

# ዋቢ ድረ-ገጾችReference-websites

-
- (Tigray Regional State, Five Years 2010/11-2014/15, Growth & Transformation Plan, Bureau of Plan and Finance, September 2003 E.C, Mekelle, page 17)  Next Five Years (2010/11-2014/15) Regional GTP: Tigray Region Plan and Finance Bureau


**Department Address**
**Ministry of Foreign Affairs**
**Diaspora Engagement Affairs General Directorate**
**P. O. Box 393**
**Tele +251 115 51 38 84, +251 115 51 73 45**
**Fax +251 115 51 43 00**
**E-mail: diaspora@mfa.gov.et**
**mfa.community@ethionet.et**
**Addis Ababa, Ethiopia**



- Ethiopia.gov.et- Your Connection to Government

- DISCOVER ETHIOPIAYour Home Land
- COUNTRY PROFILEECONOMYHISTORYTHE FEDERAL GOVERNMENTREGIONAL STATESABOUT USDiaspora Co. Offices
- THE DIRECTORATE GENERALSERVICE PROVIDEDFEDERAL DIASPORA CO. OFFICESREGIONAL DIASPORA CO. OFFICETHE DIASPORA POLICY
- ETHIOPIAN ORIGIN ID DIASPORA ACCOUNT THE GERD BONDNEWS & EVENTSLatest News & Events
- NEWSDIASPORA INFORMERARTICLES & NEWSLETTER UPCOMING EVENTSDISPORA IN ACTIONYour Efforts & Opinions
- PROMINENT DIASPORA INTRADE & INVESTMENT KNOW. & TECHNOLOGY TRANSFERIMAGE BUILDING YOUR OPINION MATTERSDIASPORA FORUMDIASPORA CORNERFREQUENTLY ASKED QUESTIONSINVESTMENT INFORMATIONInvestment Guide & Profile
- INVESTMENT GUIDETHE OPERATING ENVIRONMENTINVESTMENT OPPORTUNITIESINVESTMENT PROCEDURESINVESTMENT INCENTIVESBUSINESS INFORMATIONBusiness, Customs & Tax Info
- BUSINESS REGISTRATION GUIDECUSTOMS PROCEDURE & GUIDETAXATION PROCEDURE & GUIDEየትግራይ ክልል የዳያስፖራ የመኖሪያ ቤት ልማት ፐሮግራም መመሪያ